# ወርሃዊ የአየር ጠባይ

# ግምገማ እና ትንበያ መጽሔት

## ከኖቬምበር 1-30 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ እንዲሁም ከዲሴምበር 1-31/2024 የሚኖረው ወርሃዊ የአየር ጠባይ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ዲሴምበር 2024

አዲስ አበባ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ርዕስ


እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2024 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ ....- 1 -

ምስል፡1 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው ስፍራዎች ....- 2 -

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ....- 4 -

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ....- 4 -

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ....- 4 -

እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2024 የነበረው የአየር ጠባይ በግብርና ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ - 5 -

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ....- 5 -

እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2024 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ..- 6 -

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ....- 6 -

እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ ....- 7 -

ካርታ 6 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1-31፣ 2024 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ....- 7 -

እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ....- 8 -

እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ....- 8 -




ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2024 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ

በኖቬምበር ወር በሁለተኛው እና ሶስተኛዉ አሥር ቀናት ወደ ሀገራችን ሲገባ የነበረዉ ዕርጥበት አዘል አየር ከመጠናከሩ ጋር ተያይዞ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በደቡብና ደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ ክፍሎች ላይ ዝናብ በቦታና በመጠን ረገድ የተሻለ ነበር፡፡ እንዲሁም ለዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታ የሚፈጥሩ የአየር ሁኔታ ክስተቶች መጠናከር በማሣየታቸው ምክንያት በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከነበራቸው የደመና ሽፋን በመጠንም ሆነ በስርጭት የተሻለ ዝናብ የነበራቸው ሲሆን፤ በተለይም በዚህ ወቅት በመደበኛ ሁኔታ ደረቃማ የአየር ሁኔታ የሚስተዋልባቸዉ የሰሜን፣ የሰሜን ምስራቅ፣ የመካከለኛዉ እና የምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ወቅቱን ያልጠበቀ ከቀላል  እስከ መከከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ተስተውሏል፡፡  በተጨማሪም አልፎ አልፎ ከነበረዉ የደመና ክምችት የዝናቡ መጠንና ስርጭትም በተለያዩ ቦታዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ  በአንዳንድ ስፍራዎች ላይ የተመዘገበ ሲሆን፤ በጥቂት ቦታዎች ላይም ከባድ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡


በአጠቃላይ በኖቬምበር በወሩ ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው ጣቢዎች ለመጥቀስም ያህል ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ከመዘገቡ ጣቢያዎች መካከል ለመጥቀስ ያህል አዲግራት 55፣ አሊ.ያ 49.1፣ አማን 32.5፣ 39.4 አንገር ጉትን 30.6፣ አሶሳ 43.8፣ አዋሽ አርባ 55፣ 60፣ ባህርዳር 54.2፣ ቡለን 30.5፣  ቻግኒ 37.1፣ ጭራ 44፣  ደባርቅ 35፣  ቢሾፍቱ 33.8፣ 33.8፣ ጋምቤላ 31.3፣ ጊዲ አያና 39.7፣ 56.1፣ ጊኒር 64፣ጎሬ 47.2፣ 31.3፣ ሀረሪ 37፣ ሆስዕና 45፣ ኮንሶ 42፣ 31.5፣ ላሬ 50፣ ሊሙ ገነት 44.6፣ ማሻ 30.1፣ መኢሶ 34፣  መተሐራ 58.1፣ 78.5፣  ሞታ 34፣ ነገሌ 36.1፣ ነቀምቴ 33፣  ኑራ ኤራ 51.9፣ ቲፒ 33.4 እንዲሁም ወራቤ 96.0 በሚ.ሜ ይገኙበታል፡፡ በሌላ በኩል የሌሊትና የማለዳው ቅዝቃዜ እምብዛም ያልተጠናከረ ቢሆንም፤ የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን በአንዳንድ የሀገሪቱ ደጋማ ስፍራዎች ላይ ከ5 ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ለአብነትም በቢሾፍቱ 4.5፣ 2.0 እና 4.8፣ በአዲግራት 4.0፣ በሃሮማያ 3.8፣ 3.6፣ እና 4.2፣ በአለም ከተማ 4.8፣ 4.5 እና 3.4፣ በአምባ ማርያም 4.6፣ 3.4፣ 3.4፣ 4፣ 4.6፣ 4.6፣ 4.0፣ 2፣ 3.6፣ 4፣ 4.2፣ 4.4፣ 4.4፣ 4.8፣ እና 4፣ በአርሲ ሮቤ 4.5፣ 3.5፣ እና 4.5፣ በባቲ 4.6፣ በቡኢ 4.0፣ 4.6፣ 3.6፣ 3.6፣ 2.0፣ 2.6፣ 3.0፣ 4.6፣ 4.8፣ 4፣ 4.6 እና 4.6፣ በደባርቅ 5.0፣ በደብረ ብርሃን 4.0፣ 4.0፣ 4.6፣ -1.8፣ -0.2፣ 2.0፣ 4.8፣ 3.8፣ 3.2፣ 3፣ 3.6፣ 3.2፣ 4.2፣ 3. 4፣ እና 3.2፣



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

በእነዋሪ 2.5፣ 2.4፣ እና 2.5፣ በጅግጅጋ 1.5፣ 1.0፣ ፣1.4፣ 3.6፣ 4.8፣ 2.4፣ 2.4፣ 4.3፣ እና 3.6፣ በማይጨዉ 4.5፣ በመሀል ሜዳ 4.2፣ 0፣ 0.6፣ 4.8፣ 3.6፣ እና 3.2፣ በሾላ ገበያ 2.0፣ 2.0፣ 2.1፣ 4.0፣ 4.1፣ 2.1፣ 2.0፣ 3.0፣ 2.1፣ 2፣ 2.1፣ 2.1፣ 2፣ 2፣ 1.2፣ 2.1፣ እና 2 በወገል ጤና 4.8፣ 1.5፣ 2.0 2.4 እና 4.5፣ በወረኢሉ 4.2፣ እና 4.8 እንዲሁም በየትኖራ 4.8 በዲግሪ ሴልሽየስ ይገኙበታል፡፡

በአጠቃላይ በኖቬምበር ወር በ30 የተለያዩ የሀገሪቱ ጣቢያዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለው የዝናብ መጠን ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ የሀገሪቱ ጣቢያዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 42 እስከ 96 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከ50 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሀገሪቱ አከባቢዎች መካካል  በወራቤ፣ በመተሐራ፣ በጊኒር፣ በአዋሽ አርባ፣ በጊዲ አያና፣ በአዲግራት፣ በባህር ዳር፣ በኑራ ኤራ፣  እንዲሁም በላሬ ይጠቀሳሉ (ምስል 1) ፡፡




ምስል፡1 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው ስፍራዎች



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ባለፈዉ የኖቬምበር ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም በተለይም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት ከኦሮሚያ ክልል ጉጂና ምዕራብ ጉጂ፣ ቦረናና ምስራቅ ቦረና፣ ባሌና ምስራቅ ባሌ፣ አርሲና ምዕራብ አርሲ፤ ከሶማሌ ክልል የሊበን፣ የዳዋ፣ አፍዴር፣ የሸበል፣ የነጎብ፣ የቆራሂ የዶሎ፣ የኤረር እና የጃረር ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጌዲኦ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ቡርጂ፣ ኮንሶ፣ አሊ እና ባስኬቶ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች ከ31-120 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ5-22 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸው:: በተጨማሪም ከክረምት ወቅት ጀምሮ ዝናብ እያገኙ የነበሩት የሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፤ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ቄለም ወለጋ፣ ጅማ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የምዕራብ፣ የደቡብ፣ የማዕከላዊና የሰሜን ጎንደር፣ የአዊ ዞን፣ ምዕራብ፣ ምስራቅና ሰሜን ጎጃም፤ የሰሜን ምዕራብና የምዕራብ ትግራይ ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የመተከል፣ የአሶሳ፣ የካማሺ እና የማኦ ኮሞ ልዩ ዞን፤ ከጋምቤላ ክልል የኢታንግ ልዩ ዞን፣ ኑዌር፣ አኝዋክ እና ማዣንግ ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ዳውሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ኮንታ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች ላይ ከ51-140 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ7-18 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸው፡፡


በሌላ በኩል የበጋ ዝናብ ተጠቃሚ ባልሆኑት አከባቢዎች ማለትም በደቡብ፣ በደቡብ ምስራቅ፣ በምስራቅና በመካከለኛዉ ትግራይ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የደቡብ ወሎ እና የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ የዋግህምራ ዞን፤ ከአፋር ክልል ቅልበቲ፣ የማሂ፣ ጋቢ፣ ሃዉሲ እና ሃሪ ዞኖች ላይ ከ11-50 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ2-6 ቀናት ያህል ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ተመዝግቧል (ካርታ 1 እና 2) ፡፡

ባለፈዉ ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት ከኦሮሚያ ክልል ጉጂና ምዕራብ ጉጂ፣ ቦረናና ምስራቅ ቦረና፣ ከሶማሌ ክልል የሊበን፣ የዳዋ፣ አፍዴር፣ ኖጎብ፣ ኤረር አና ጃረር ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጋሞ፣ ጎፋ፣ ጌዲኦ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ቡርጂ፣ ኮንሶ፣ አሊ እና ባስኬቶ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ አግኝተዋል (ካርታ 10)፡፡ በተጨማሪም ከክረምት ወቅት ጀምሮ ዝናብ እያገኙ የነበሩት የሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፤ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ቄለም ወለጋ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የምዕራብ፣ የደቡብ፣ የአዊ ዞን፣ ምዕራብ ጎጃም፤ የሰሜን ምዕራብና የደቡብ ምስራቅ እና ምስራቅትግራይ ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የመተከል፣ የአሶሳ፣ የካማሺ እና የማኦ ኮሞ ልዩ ዞን፤ ከጋምቤላ ክልል የኢታንግ ልዩ




ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et


ዞን፣ ኑዌር፣ አኙዋክ እና ማዣንግ ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ዳውሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ኮንታ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች ከመደበኛ በላይ ዝናብ አግኝተዋል (ካርታ 3) ፡፡




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት





ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2024 የነበረው የአየር ጠባይ በግብርና ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የኖቬምበር ወር በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ የእርጥበት ሁኔታ ተስተውሏል። ይህም ሁኔታ ሰብል በደረሰባቸው አካባቢዎች ለሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባ አመቺ ሁኔታን የፈጠረ ነበር፡፡ በሌላም በኩል በምራብ፣ በሰሜን ምራብ እና በደቡብ ምራብ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የነበረው እርጥበት ሙሉ ለሙሉ እድገታቸውን ላልጨረሱ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች፣ ለፍርፍሬ ተከሎችና ለጓሮ አትክልቶች የውሃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም በመኸር ወቅት መጨረሻ ላይ በአፈር ውስጥ በተከማቸ እርጥበት በመታገዝ ለሚዘሩ እንደ ጓያ እና ሽንብራ ለመሳሰሉ የጥራጥሬ ሰብሎች ጠቀሜታ የነበረው ቢሆንም በተለይም በዚህ ወቅት በመደበኛ ሁኔታ ደረቃማ የአየር ሁኔታ የሚስተዋልባቸዉ የመካከለኛዉ፣ የምስራቅ እና የሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ አልፎ አልፎ የነበረው ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ በተለይም በደረሱ እና በመሰብሰብ ላይ በሚገኙ ሰብሎች ላይ በመጠኑም ቢሆን አሉታዊ ተጽዕኖ ነበረው፡፡ በአንጻሩም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብ፣ የደቡብ ምዕራብ እና የደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የነበረው እርጥበት በተለይም በደጋማው አካባቢ በቦረናና ጉጂ ዞኖች ለተዘሩ ሰብሎች ምቹ ሁኔታ የፈጠረ ሲሆን በአርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደሮች አካባቢ ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻልና የዝናብ ውሃን ለመሰብሰብና ለማከማችት ገንቢ ሚና ነበረው (ካርታ 4)፡፡





ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2024 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የኖቬምበር ወር የነበረው የአየር ጠባይ በውሃ ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ስንመለከት በአብዛኛው ባሮ አኮቦ፣ ኦሞ ጊቤ፣ አባይ፣ ገናሌ ዳዋ፣ በላይኛው እና መካከለኛው አዋሽ፣ ዋቢ ሸበሌ፣ በመካከለኛው እና ታችኛው ስምጥ ሸለቆ እና በጥቂት በመካከለኛው ተከዜ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ ከፍተኛ እርጥበት ነበራቸው፡፡ ይህ ሁኔታ ለገፀምድር ውሃ ሀብት መጎልበት አውንታዊ ጎን እንደነበረው የተተነተኑ የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ በሌላ በኩል በአብዛኛው አፋር ደናክል፣ ኦጋዴን፣ በታችኛው እና በመካከለኛው ዋቢ ሸበሌ፣ ተከዜ፣ የታችኛው አዋሽ እንዲሁም የታችኛው አባይ ኪስ ቦታዎች ላይ ደረቅ ሁኔታ ስር ቆይተው ነበር(ካርታ 5) ፡፡





ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ

በሚቀጥለው የዲሴምበር ወር ዝናብ ሰጪ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ቀጣይነት እንደሚኖራቸዉ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብና በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ቀላል መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸዉ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በተጨማሪም በጸሀይ ኃይል ታግዘው ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በምስራቅ፣ በሰሜን ምስራቅ፣ በሰሜን፣ በሰሜን ምዕራብ እና በምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት ወቅቱን ያልጠበቀ አነስተኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ይኖራል (ካርታ 6) ፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1-31፣ 2024 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## ኢ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥለው ወር በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የሚኖረው ደረቅ የእርጥበት ሁኔታ፤ በተለይም የመኸር ሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራትን ለማከናወን አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ በሌላ በኩል አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት በተለይም በደቡብና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የሚጠበቀው ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው እርጥበት የበጋ ወቅት ሰብል ለሚያመርቱ ጥቂት የደቡብ ኦሮሚያ አካባቢዎች አዎንታዊ ሚና የሚኖረው ሲሆን፤ በተጨማሪም ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት በጎ ጎን ይኖረዋል፡፡ በሌላ በኩል በመካከለኛው፣ በምስራቅ እና በሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ በደረሱና ሙሉ በሙሉ ባልተሰበሰቡ ሰብሎች ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያስከትል ስለሚችል አርሶ አደሮችም ሆኑ የሚመለከታቸው አካላት ባሉት ደረቅ ሰሞናት የሰብል ስብሰባ ተግባራትን አጠናክረው እንዲያከናውኑ ኢንስቲትዩቱ ይጠቁማል።

## ኢ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥለው የዲሴምበር ወር በአብዛኛው ባሮ አኮቦ፣ በመካከለኛዉ እና ታችኛው ኦሞ ጊቤ፣ በታችኛው ስምጥ ሸለቆ፣ አባይ፣ ገናሌ ዳዋ፣ ተከዜ እና ዋቢ ሸበሌ ተፋሰሶች ላይ መካከለኛ መጠን ያለው እርጥበት የሚያገኙ ሲሆን፤ ይህ ሁኔታ የገፀምድር የውሃ ሀብትን በመጠኑ እንደሚያሻሽል ይጠበቃል። በተለይም አብዛኛዎቹ ግድቦች አሁናዊ የውሃ መጠናቸው ከመደበኛው የተቀራረበ እና በተወሰኑት ላይ ከፍ ያለ በመሆኑ በቀጣይ የሚጠበቀው እርጥበት ለሀይል ማመንጫም ሆነ ለበጋ መስኖ ውሃ አቅርቦት አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል። በመሆኑም የሚመለከታች አካላት በተለይም በእርጥበት አጠር አካባቢ የሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚገኘውን እርጥበት በማከማቸት የተሻለ የውሃ አቅርቦት እንዲኖር የሚያስችል ተግባራትን እንዲያከናውኑ ይመከራሉ፡፡ በሌላ በኩል በአብዛኛው አዋሽ፣ አፋር ደናክል እና አይሻ ተፋሰሶች ደረቅ ሁኔታ ስር ይቆያሉ፡፡



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et